በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ግንቦት 14 ቀን 2011 ዓ/ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

## ኢትዮጵያ አንድ አዲስ ለተገኘ ግዙፍ የሕዋ አካል ስም እንድታውጣ ዕድሉ ተሰጣት

ኢትዮጵያ ሀገራችን አሁን ያለችበት ሁለንታናዊ ልዉጥ የበርካታ ሀገራትንና ድርጅቶችን ቀልብ እየሳበ ይገኛል። በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያ እንድትሰይም ዕድሉን የሰጣት፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር አባል የሆነችበት ዓለም አቀፉ የሕዋ ኅብረት (IAU- International Astronomical Union)።

ኢትዮጵያ ስም እንድትሰጠው የተወሰነው የሕዋ አካል ሳይንሳዊ መለያ ቁጥሩ HD 16175 ና HD 16175 B የተሰኘው የራሷ ፀሐይ ያላት፣ ጸሐይዋን የሚዞሩ ፕላኔቶች የያዘ ሥርዓት (planetary system) ነው። ኢትዮጵያ በተሰጣት ዕድል መሠረት እንደ ሀገር ተገቢውን መሥፈርት አሟልታ ተገቢውን ስያሜ ሰጥታ፣ ይህም ስያሜ ዓለም አቀፍ ተቀባይነትን ካገኘ፣ ስያሜው ለዝንተ ዓለሙ የሚዘልቅ ነው።

በመሆኑም ለሀገራችንና ለህዝቦቿ የተለየ ታሪካዊ እድል ነው። በመሆኑም መላው የሀገራችን ሕዝብ ለዚህ ዕድል በመብቃታችን እንኳን ደስ አለን እያልን የሚጠበቅብንን ሙሉ በሙሉ አሳክተን ስያሜውም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት አግኝቶ ለኢትዮጵያም ሆነ ለመላው የሰው ልጅ ለዝንተ ዓለሙ የኢትዮጵያን አሻራ ይዞ የሚዘልቅ ስያሜ እንዲሆን ኢትዮጵያዉያን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያሉ የሀገራችን ሕዝብ ተቋማት የሆኑት በሙሉ፣ ማለትም የመንግሥት መ/ቤቶች፣ ከአነስተኛ እስከ ታላላቅ የግል ድርጅቶች፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ልዩ ልዩ አይነት ማኅበራት፣ ዩኒቨርስቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ ላይ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት፣ የምሁራን መድረኮች፣ በዓለም ላይ በየትኛውም ቦታ የሚገኙ ዜጎቻችን፣ እድሮች፣ ትውልደ ኢትዮጵያዉያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ስም በማዉጣቱ አኩሪና ታሪካዊ ሂደት ከልባችሁ እንድትሳተፉ ይህ ሀገራዊ ጥሪ ቀርቦላችኋል።

**ለመሳተፍ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀዉ የስልክ መሥመር 920 ላይ ስያሜዎን በጽሑፍ በመላክ የዚህ ዕድል ተሳታፊ ይሁኑ።**

//